የሰ/መ/ቁ. 58514

ጥር 9 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሐንካራ ሐርቃ ሃያሞ

**ተጠሪ፡-** የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ

መርዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የአሁኑ አመልካች በወንጀል የተከሰሱበትን ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ባለቤት ሆኖ መገኘት ጉዳይ በሚመለከት በይግባኝ ደረጃ ቀርቦለት የተመለከተው የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው የጥፋተኛነት ፍርድ እና የቅጣት ውሣኔ ላይ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ የቀረበውን ክርክር በመጨረሻ ያየው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 39818 በ22/10/2002 የጥፋተኛነቱም ሆነ የቅጣት ውሣኔው እንዲሁም የንብረት መወረስ ውሣኔው በአግባቡ ስለሆነ ፀንቷል በሚል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በሚል በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10(3) መሠረት የቀረበ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ሐምሌ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ነው በመባሉ ማመልከቻው ለተጠሪው ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በ08/03/2003 ጽፎ ባቀረበው መልስ በዚህ ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ምንም አይነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ አመልካች ለሰበር ባቀረቡት ማመልከቻ ላይ በሥር ፍ/ቤት የህግ ስህተት ተፈጽሟል ብለው የገለጿቸው ምክንያቶች ስለማስረጃ ምዘናና ከጥፋተኛነቱ ውሣኔ በኋላ ስላሉ ጥቃቅን ፍሬ ነገሮች የሚመለከቱ እንጅ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመኖሩ የሚያስረዱ አይደሉም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንዲህ አይነት የማስረጃ እና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በሕጉ የማየት ስልጣን የለውም በማለት የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሆኖ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲፀና ጠይቋል፡፡

በአመልካች ጠበቃ በኩልም የመልስ መልስ መቅረቡን መዝገቡ ያሳያል፡፡

ይህ ችሎትም የአሁኑ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 419 ላይ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ በእጃቸው ገብቶ ተገኝቷል ተብለው በወንጀል የተከሰሰባቸውን ጉዳዮች በሚመለከት በሥር ፍ/ቤት ታይቶ በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ሲመረምር መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡ በተለይ ቅጣቱን በተመለከተ የአሁኑ አመልካች በመንግሥት ሥራ ላይ ሆነው ከብር 182 የወር ደመወዝ ተነስተው በጭማሪና በዕድገት ብር 928 የወር ደመወዝ ላይ ደርሰው በዚህ መጠነኛ ደመወዝ ራሣቸውን ሲያስተዳድሩ እንደቆዩና ባለቤታቸውም ሌላ ህጋዊ ገቢ እንዳልነበራቸው እየተገለፀ ምንጩ ያልታወቀ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በእጃቸው ገብቶ መገኘቱና ከፍተኛ ግምት ያለው ንብረት ባለቤት ሆነው መገኘታቸው ነገሩን ከባድ ስለሚያደርገው በዚሁ በሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው እስከ አምስት አመት ከሚደርሰው የጽኑ እስራት ቅጣት በአራት አመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ መወሰኑ ያለአግባብ ቅጣቱ ከብዶባቸዋል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በመ/ቁ 39816 በ22/10/2002 የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ፀንቷል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ራ/ታ